# ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ)

# NILE INSURANCECOMPANY (S. C)

## የስብሰባ ጥሪ

## ለናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

**የማኅበሩ ዋና ገንዘብ፡-** ብር *1,000,000,000.00 (አንድ ቢሊየን ብር)*

**የማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር፡-** 980/2008

**የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚገኝበት፡-** *አዲስ አበባ፣* *ንፋስ ስልክ ላፍቶ* **ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ** *08፣* **የቤት ቁጥር** *1721*

በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013፣ አንቀጽ 366(1)፣ 370 እና 393 እንዲሁም በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 8 መሠረት የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 26ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ኅዳር 1 ቀን 2016 ዓ/ም ብሔራዊ ትያትር አጠገብ በሚገኘው እና በመጠናቀቅ ላይ ባለው የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት 24ኛ ፎቅ ላይ ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡
በመሆኑም ውድ የማኅበራችን ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔዎቹ ላይ እድትገኙለት የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት አስተላልፏል፡፡

## የ29ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ረቂቅ አጀንዳ፡

ድምጽ ቆጣሪዎች ተለይተው ምልዐተ-ጉባዔው መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ፡-

1. የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
2. ከኅዳር 24 ቀን 2015 ዓ፣ም. ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ፣ም. ድረስ የተከናወኑ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማሳወቅ፤
3. እ.አ.አ የ2022/23 የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይ ማጽደቅ፤
4. እ.አ.አ የ2022/23 የውጪ ኦዲተሮችን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይ ማጽደቅ፤
5. እ.አ.አ የ2022/23 በጀት ዓመት ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
6. እ.አ.አ ለ2022/23 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዓመታዊ የሥራ ዋጋ መወሰን፤
7. እ.አ.አ ለ2023/24 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ወርሃዊ አበል መወሰን፤
8. እ.አ.አ የ2023/24 በጀት ዓመት የውጪ ኦዲተሮችን የአገልግሎት ክፍያ መወሰን፤
9. የቦርድ ምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ዓመታዊ የአገልግሎት ዋጋ መወሰን፤
10. አሁን በሥራ ላይ ያለውን የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚተኩ የቦርድ አባላትን መምረጥ፤
11. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ፡፡

## የ26ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ረቂቅ አጀንዳ፡

1. የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
2. ከተከፈለው የማኅበሩ ካፒታል ዕድገት አንጻር መመስረቻ ጽሑፉን ማሻሻል፤
3. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

- በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ከሆነ በወኪልዎ አማካኝነት መሳትፍ ይችላሉ፡፡

**በወኪል የሚሳተፉ ከሆነ፡**

- ከጉባኤው ሦስት (3) ቀናት በፊት ጎተራ በሚገኘው የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት 1ኛ ፎቅ በግንባር ቀርበው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው እዲፈርሙ ወይንም
- ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን የያዙ ተወካይ በዕለቱ በጉባኤው ቦታ የሰነዱን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን ይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ ለመሳተፍ ይችላሉ፡፡

- ባለአክሲዮኖችም ሆኑ ወኪሎች ወደ ስብሰባው ቦታ ሲመጡ ማንነታቸውን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ ወይንም መንጃ ፈቃድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- እሑድ መስከረም 27 ቀን 2016 ዓ.ም በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የተላለፈው የስብሰባ ጥሪ በዚህ ተተክቷል፡፡

**ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**